በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን።

# ለሙታን የሚደረግ ጸሎት - ጸሎተ ፍትሐት

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

ሚያዚያ ፳፭ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.

# ጸሎተ ፍትሐት

*መግቢያ*

- ፍትሐት ማለት ከኃጢአት እስራት መፍታት ወይም መፈታት ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ለሞቱ ሰዎች የሚደረገው ጸሎት፣ ጸሎተ ፍትሐት ይባላል፡፡

- ቅድሳት መጻሕፍትን የቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት በማድረግ የሙታን ነፍሳት ከሥጋ እንደተለዩ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በማረፊያ ቦታ ይቆያሉ እንጂ በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ ወይም ወደ ገሃነመ እሳት እንደማይላኩ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው ትምህርት ነው፤ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ የሚቆዩበትም ቦታ ለጻድቃን ገነት ሲሆን ለኃጢአተኞች ደግሞ ሲኦል ነው፡፡ የጻድቃን ማረፊያ ቦታቸው ገነት መሆኑን ለማመልከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረ ጊዜ ንስሐ ለገባው ወንበዴ፡ "በእውነት እልሃለው … ዛሬውኑ ከእኔ ጋር በገነትትሆናለህ" ብሎታል (ሉቃስ ምዕራፍ 23 ቁጥር 43)፡፡ የኃጢአተኞች መቆያ ደግሞ ሲኦል መሆኑን ለማመልከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሀብታሙ ሰውና በድኻው አልዓዛር ምሳሌ ትምህርቱ … ሀብታሙ ሰው በሲኦል ውስጥ እንደነበረ ገልጾአል፡፡ *ሉቃስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 23*፡፡

- በሙታን ትንሣኤ ጊዜ የምንነሳው በውርደት ወይም ክብር በሌለው ሁናቴ በመሬት ውስጥ እንደተቀበርነው ሳይሆን፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው በክብር፣
በኃይልና
በመንፈሳዊነት ነው (1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 42 እስከ 44)፡፡ ከዚያም በኋላ ወደ ክርስቶስ የፍርድ ፊት እንቀርባለን፡፡ *2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 10*፤ *ራዕይ 6፡9-11*፡፡

# ጸሎተ ፍትሐት...

- ይቅርታ በዚሁ ዓለምና በሚመጣው ዓለም መኖሩን ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል፡፡ ማቴዎስ 12፡32፡፡

- ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ለነበረው ለኦኔሲፎር "በመጨረሻው ቀን ምሕረትን ይስጠው" ብሎ ጸልዮለታል፡፡ 2ኛ ጢሞቴዎስ 1 ፡18፡፡ ለሞቱ ሰዎች ስለሚያስፈልጋቸው ታላቁ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሞተው ሰው ለኦኔሲፎር ጸልዮለታል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ይህንኑ ጸሎት ለሞቱ ሁሉ ትጸልያለች፡፡

*ጸሎተ ፍትሐት በአይሁድ*

- ለሞቱ ሰዎች መጸለይ ደግሞ በጥንት በዘመነ ብሉይም ነበረ፡፡ ጀግናው ይሁዳ መቃብዮስ በጦርነት ለሞቱ ወታደሮቹ የኃጢአት መሥዋዕት ይደረግላቸው ዘንድ ሁለት ሺህ የብር ድራህም አሰባስቦ ወደ ኢየሩሳሌም ልኮአል፡፡ 2ኛ መቃብያን 12 ፡43፤ ዕዝራ ሱቱኤል 6:35-…፡፡ አይሁድ ለሙታን ሲጸልዩ ዳዊት ይደግማሉ፡፡

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ላይ ባደረገው ስብከቱ እንዲህ ብሏል "አንድ ሰው ኃጢአተኛ እንደሆነ ቢሞት የምንችለውን ያኽል ልንረዳው ይገባል፡፡ የምንረዳውም በለቅሶና በሐዘን ሳይሆን በጸሎት፣ በምጽዋትና በቁርባን ነው፡፡ የዓለምን ኃጢአት ወደ ተሸከመው የእግዚአብሔር በግ ስለ ሙታን የምንጸልየው እነርሱ መጽናናትንና ዕረፍትን እንዲያገኙ ብለን ነው እንጂ በከንቱ አይደለም፡፡ ጻድቁ ኢዮብ ስለልጆቹ ያቀርብ የነበረው ቁርባን ጠቀሜታ ከነበረው ስለ ሙታን የምናቀርበው ቁርባን ምንኛ የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረው?;

# ጸሎተ ፍትሐት የሚደረግላቸው እነማን ናቸው?

- ጸሎተ ፍትሐት የሚደረግላቸው [illegible] ኃጢአቶቻቸው [illegible] የተፈጸሙ ኃጢአቶች፣ እንዲሁም ለተረሱ ኃጢአቶችና ኃጢአት ሰሪው ኃጢአት መስራቱ ሳይሰማው የሚሰራቸው ኃጢአቶች ናቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉት ኃጢአቶች ከሰው ተፈጥሮ ደካማነት የተነሳ የተፈጸሙ መሆናቸው ቢታመንበትም በእግዚአብሔር ፍትሕ በኩል ግን እንዲህ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረው “አንድ ሰው ባለማወቅ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ አንዱን ቢተላለፍ በደለኛ ነው” ብሎ ነው፡፡ *ዘሌዋ 5 ፡17፡፡*

- ሰው አፈር የሆነውን ሥጋ የለበሰ እንደሆኑ መቼም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ከኃጢአት የነፃ ሊሆን አይችልም፡፡ “ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን፣ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም” የሚለው ነው፡፡ *1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 8*፡፡

- እግዚአብሔር በንስሐ የሚመለሰውን ሰው በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ይቀበለዋል፡፡ ለምሳሌ በሞት አፋፍ ላይ የነበረውና ከጌታችን ጋር ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ ንስሐው ተቀባይነት ያገኘው በመጨረሻው ደቂቃ ነው፡፡ ስለዚህ ንስሐ የገባ ሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው ማን እንደሆነ ስለማናውቅ ለሁሉም እንጸልያለን፡፡ በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያን በፍትሐት ጸሎት አምና ትሰራበታለች፣ ይህንኑም ታስተምራለች፡፡

- ጸሎተ ፍትሐት አትግደል የሚለውን ሕግ ተላልፈው ራሳቸውን ላጠፉ ሰዎች አይፈጸምላቸውም፡፡ ይሁዳ ጌታን ከሸጠ በኋላ የገጠመው ይኸው ነው፡፡ *ዘጸአ 20፡13፤ ዘዳግ 5፡17፤ ማተ 5፡21፡፡*

- ሰው የሕይወቱ ጌታ አይደለም፡፡ እኛ በደም የተገዛን የክርስቶስ ስለሆንን የእኛ የሌሆነውን

# ለሙታን የሚደረግ ጸሎት

## የሰው ልጆች ከሞት በኋላ ያለው ዕድላቸው

- ሞት በምድር የሚኖሩ የሰው ልጆች የምድር ኑሮ መጨረሻ ነው፡፡ የመጣብንም በአዳምና በሔዋን በደል ምክንያት ነው፡፡ ዘፍጥ 2፡17፡፡

- የሰው ሞት የማንነቱ ሙሉ ለሙሉ መጥፋት ሳይሆን የለበሰው ሥጋ ወይም የአካሉ መርገፍ ነው፡፡ #ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና፡፡; የሚለው የሚመለከተው የሰውን አካል ወይም ሥጋ ነው፡፡ ዘፍጥ 3፡19፡፡

- የእግዚአብሔር መልክ በውስጥዋ የሚገኝባት ነፍስ ግን ዘላለማዊት ናት፡፡ #አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፥ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ፡፡; መክብብ 12፡19

- ነፍስ ከሥጋ ከተለየች በኋላ ነፍስ ማሰብዋን፣ መስማትዋን፣ መንቀሳቀስዋን ከዚህ ቁሳዊ ከሆነው ዓለም በተለየችው ሌላኛዋ የእግዚአብሔር አገር ትቀጥላለች፡፡

- የሰው ልጅ ሕይወት የታደለችው እንዴት ማመን፣ በጎ ሥራን መሥራት፣ ችሎታውን ማዳበር እንዳለበት… እንዲማርበት ነው፡፡ እነዚህም ሰማያዊ ሀብታትን መዝገብን ማከማቻ ይሆኑትም ዘንድ ነው፡፡

# ለሙታን የሚደረግ ጸሎት...

- የሰው ሕይወት የምድር ኑሮው በሞት ሲጠናቀቅ ነፍሱ በእግዚአብሔር ፊት ለመጠየቅና ቅጣቷን ወይም ሽልማትዋን ለመቀበል ትቀርባለች፡፡ ከአካል የተለየችውም ነፍስ ብቻዋን ቀርባ ወዲያውም የምትቀበለው ፍርድ ከሥጋ ለተለየች ነፍስ ብቻዋን የምትቀበለውና የመጨረሻም ያልሆነ ፍርድ ነው፡፡ *1ኛ ሳሙ 2፡6፡፡*
#ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፡፡; *ዕብ 9፡27፡፡*

- በዓለም ፍጻሜ ሙታን ሁሉ ከተነሡ በኋላ በሁሉም የሰው ዘር ላይ እግዚአብሔር በአንድ ላይ እንደሥራቸው ይፈርዳል ይፈርድላቸዋል፡፡

- ሰውም ከሞት ተነስቶ በሚለብሰው አካሉና ነፍሱ ዘላለማዊ ሽልማቱን ወይም ፍርዱን ይቀበላል፡፡

- ከመጨረሻው ፍርድ በፊት አስቀድሞ በሚያገኘን የሥጋ ሞት የጻድቃን ነፍሳት ወደ ገነት ሲገቡ ኃጥአን ደግሞ ወደ ሲኦል ይወርዳሉ፡፡ እነዚህም ጊዜያዊ መቆያዎች ናቸው፡፡

- ሰው በሕይወት በምድር ሲኖር ንስሐ የሚገባበትና የቀድሞ ጥፋቱን የሚያርምበት ዕድል በእግዚአብሔር ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ዕድል ግን ከሞት በኋላ ይነጠቃል፡፡

# ለሙታን የሚደረግ ጸሎት...

- እስከ መጨረሻው የፍርድ ቀን ኃጥአን የሚቀጡት ቅጣት ጊዜያዊና ሊቀልም የሚችል ነው። በተጨማሪም ቤተክርስቲያንና ካህናቱ ከምዕመናኑ ጋር በሚጸልዩላቸውም ጸሎት በእግዚአብሔር ፈቃድ ከሲኦል የመውጣት ዕድልም ያለበት ነው። #እግዚአብሔር ይገድላል ያድናልም ወደ ሲኦል ያወርዳል፥ ያወጣል።; 1ኛ ሳሙ 2፡6።፤ #አቤቱ፥ ነፍሴን ከሲኦል አወጣሃት; መዝ 30፡3፤ #በታች ካለው ከሲኦል ያመልጥ ዘንድ የሕይወት መንገድ አስተዋዩን ሰው ወደ ላይ ይወስደዋል።; ምሳሌ 15፡24፤ #ወደ ሲኦል ቢወርዱ እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች; አሞጽ 9፡2፤ #በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ።; ሉቃ 16፡23፤ #ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።; ራዕይ 1፡18።

- ለሙታን የሚደረግ ጸሎት - ጸሎተ ፍትሐት ዘወትር ጠቃሚ ነው። ወደ ገነት ለመግባት ላልታደሉት ጸሎቱ ዕድላቸውን ከመቃብር በላይ ያደርግላቸዋል። #በሰማይ ስማ ሰምተህም ይቅር በል።; 2ኛ ዜና 6፡21። በገነት ላሉትም እንደ ታላቅ ብርሃን እየፈነጠቀ ታላቅ ደስታን ይሰጣቸዋል።

# ለሙታን የሚደረግ ጸሎት አስፈላጊነት

- ከሞትም በኋላ ቢሆን በሰዎች መካከል የሚኖረው መንፈሳዊ ግኑኝነት በጸሎት አማካይነት ይቀጥላል፡፡ *ሉቃ 16፡19-31፡፡*

- በእምነት የሚደረግ ጸሎት ኃይል እንዳለው ተራራንም ለማንቀሳቀስ እንደሚያስችል በወንጌል ተገልጾልናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም የአንዱ ሰው ጸሎት ሌላውን እንደሚራዳ እንደረዳም ያስተምራሉ፡፡ *ዮሐ 4፡46-53፤ ማቴ 15፡21-48፤ ማር 9፡17-27፤ ማር 2፡2-12፤ ማቴ 8፡5-13፤ ዮሐ 11፡1- ... ፡፡*

- ጌታችን ከላይ ከተጠቀሱትን ተአምራት በርካታዎቹን በአካል በቦታው ተገኝቶ ሳይሆን ሳይገኝ በኃይሉ ፈጽሟል፡፡ ታዲያ ለምንጸልየው መልስ ለመስጠት ከሲኦል ወደ ገነት ያለው መንገድ ይርቀው ወይስ ይከብደው ይሆን? *1ኛ ሳሙ 2፡6፡፡* ቅዱስ ዮሐንስም አምነን በጸሎት እንድንተጋ ብቻ ያበረታታናል፡፡ #በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል፡፡; *1ኛ ዮሐ 5፡14፡፡*

- ጸሎት እንደ ብርሃን ነጸብራቅ የፍቅር ውጤት ነው፡፡ እግዚአብሔርን አምነው የሚጸልዩትን ከምድር ጫፍ እስከ ምድር ጫፍም ይሁን የእርሱ አገር እስከ ሆነውም አልፎ ያገናኛል፡፡

- ጸሎት እኛ የምንኖርባትን ዓለም ከመላእክት፤ ከቅዱሳንና በሞት የተለዩን ወገኖቻችን ከሚገኙባት ዓለም ጋር ያገናኛል፡፡

# ለሙታን የሚደረግ ጸሎት አስፈላጊነት...

- ሞት በጌታችን ትንሳኤ የተነሳም የቀደመ ኃይሉን አጥቷል፡፡ ትንሳኤውም የአዲስ ሕይወት መጀመሪያ ሆኖአል፡፡ ሮሜ 8፡38-39፡፡ በዚህም የተነሳ እግዚአብሔርን #ሁሉ ለእርሱ ሕያዋን ስለ ሆኑ፥ የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም፡፡; እያልን ሁሉ በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እንጸልያለን፡፡ ሉቃስ 20፡38፡፡

- በዚህ ዓለም የነበሩ ክርስቲያኖች በሕይወት በነበሩበት ዘመን ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር የነበረው ግኑንነት አይቋረጥም፡፡ በገነት ከሆኑ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ስለ እኛ ሊጸልዩልን ነጻነት አላቸው፡፡ ወደ ሲኦል የወረዱም ከሆኑ በዚያ ሆነው የእኛን ጸሎት ይሻሉ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን መሠረቶችዋ በምድር ሆነው ጫፎችዋ ከሰማይ ጋር የተያያዙ አድርጎ መመሰሉም ይህንኑ ለማስረዳት ጭምር ነው፡፡ #ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፥ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥ የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል፡፡; ዕብ 12፡22-24፡፡

- ይህም የሚያመለክተው በሰማይና በምድር ባሉት አብያተ ክርስቲያናት መካከል የማይጠፋ የጠበቀ ግኑኙነት ያለ መሆኑን ነው፡፡ በምንጸልየውም ጸሎት የዘመናት ገደብ ሳይኖርብን የሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን፣ የቅዱሳን ሁሉ ጸሎትም እንድትረዳን እንጸልያለን፡፡

# ያዘኑትን ማጽናናት

- ከጎናችን ያለ ሰው ሲያዝን እኛስ ማዘናችን ይቀራል? ጌታችን ወዳጁ አልዓዛር ሲሞት አዝኖለት እንባውን አፍስሷል፡፡ ይሁን እንጂ በሞት የተነሳ የሚገጥመን ሐዘን ግን በእግዚአብሔር እስከ ማጉረምረም ሊያደርሰን አይገባውም፡፡

- ሞት ለጊዜው የነፍስ ከሥጋ መለየት እንጂ የሰው ለዘላለም መጥፋት አይደለም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም እንቅልፍ እየተባለ ተጠቅሷል፡፡ *የሐ. ሥራ 13፡36፡፡*

- ይህ በሥጋ የሚገጥም አካላዊ ሞት በምድር ካለ የዘወትር ድካም፤ ሐዘን፤ ሕመም፤ ፍርሐት፤ … ይህችን ዓለም ከሞላባት ድካም ሁሉ ማረፊያ መንገድ ነው፡፡ *ራዕይ 14፡13፡፡*

- ሞት የእግዚአብሔር እውነት ብቻ ወደ ነገሰችባት፤ ሰማያዊው ብርሃን ወደ ሚያበራባት፤ የሰው ነፍስ ፍጻሜ የሌለው ደስታ ወደ ምታገኝባት ዓለም መሻገሪያ ድልድይ ነው፡፡ *1ኛ ተሰ 4፡13-14፤ 1ኛ ተሰ 4፡15-18፤፤ 2ኛ ቆሮ 5፡1-8፡፡*

- የወገኖቻችን ወደ ሌላ ዓለም በሞት መሻገር የኛም መጨረሻ መቃረቡን ያስታውሰናል፡፡ ስለዚህ መጨረሻችን ሕመምና ፍርድ የሌለበት ሰላማዊ የሆነ ክርስቲያናዊ ፍጻሜ እንዲሆንና በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እንዳይፈረድብን ለነርሱ ስንጸልይ ለራሳችንም እንጸልይ፡፡ *ሉቃ 16፡22፡፡*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።